# መሠረተቢስ ሪፖርት ይብቃን

## ክፍል አንድ

ኢ.ብሳ ነመራ 03/25/14

የአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት (US State Departement) የ2013 የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ የተመለከተ ሪፖርት ከወጣ ሁለት ሳምንት አልፎታል። የኢፌዴሪ መንግስት ባለፈው ሳምንት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያቤት ላወጣው የሰብአዊ መብት አያያዝ ሪፖርት ምላሽ ሰጥቷል። የኢፌዴሪ መንግስት የሰጠው ምላሽ በአጭሩ የሚከተለውን ይመስላል።

*የኢፌዴሪ መንግስት በሕዝብ ውክልና ስልጣን የተረከበ እንደመሆኑ መጠን የሰብአዊ መብት አያያዙን አስመልክቶ የሚቀርቡበትን ገንቢ ትችቶችና አስተያየቶች ለመቀበል ዝግጁ ነው። በመሆኑም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በ2013 የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝን አስመልክቶ ያወጣውን ሪፖርት በጥንቃቄ መርምሮታል።*

*መንግስት በአሜሪካ በኩል የእርምት እርምጃ ይወስዳል ብሎ ጠብቆ የነበረ ቢሆንም የ2013 ሪፖርት ቀደም ሲል የቀረቡ ወቀሳዎች እንዳለ የተደገሙበት፣ አዲስ ተብለው የቀረቡትም ያልተረጋገጡ መረጃዎች የቀረቡበት ሆኖ አግኝቶታል።*

*ሌላው ሪፖርቱ ላይ የሚስተዋለው ችግር "ተአማኒ" በሚል የቀረቡ የመጃ ምንጮችን የሚመለከት ነው። እነዚህ በደፈናው "ተአማኒ" ተብለው የተገለፁ የመረጃ ምንጮች የሰጡት መረጃ ማንነታቸውን አጋልጧል። የመረጃ ምንጮቹ በአገር ውስጥና በውጭ የሚንቀሳቀሱ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች ናቸው። የሕዝብ ይሁንታ የሌላቸው ሕገመንግስታዊውን ስርአት ሕገመንግስታዊ ባልሆነ መንገድ ለመናድ የሚንቀሳቀሱ ናቸው።*

ፅንፈኛ ተቃዋሚዎቹ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ያልተጨበጠ መረጃ የማቀበላቸው ዓላማ በኢትዮጵያና በአሜሪካ መሃከል በተለያዩ በርካታ ጉዳዮች ዙሪያ በመካሄድ ላይ ያለውን የሁለትዮሽ ውይይት ዋጋ ማሳጣት ነው። ሁለቱ አገራት በጋራ ከሚነጋገሩባቸው ጉዳዮች መሃከል ዋነኛው የሰብአዊ መብት አያያዝ ሁኔታ ላይ ክትትል ማድረግ የሚያስችል ውጤታማ ስልት ማዘጋጀት ነው።

ኢትዮጵያ በሰብአዊ መብት አያያዝ ረገድ መሻሻል ያሳየች ቢሆንም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የ2013 ሪፖርት ግን በተጨባጭ ካለው እውነታ የተለየ ያልተረጋገጡ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግስት ከአሜሪካ አቻው ጋር ሲያካሂድ የነበረው የሁለትዮሽ ውይይቱ አካሄድ አጥጋቢ ውጤት አላመጣም የሚል እምነት አድሮበታል።

የኢትዮጵያ መንግስት ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ሕገመንግስታዊ ግዴታ ያለበት በመሆኑ ትኩረት የሚሰጠው ለሕዝብ ደህንነት ነው። መንግስት የሕገመንግስቱን ድንጋጌዎች በማክበር ግዴታውን ይወጣ ዘንድ የሚደረግለትን ማንኛውንም ድጋፍ ለመቀበል ዝግጁ ነው። ከተሟላ የሰብአዊ መብት አያያዝ አንድሎ ሲገኝ የሚቀርብበትን ተገቢ ትችት ለመቀበል ዝግጁ የሆነውን ያህል፣ ሆን ተብሎ ገፅታውን ለማበላሸት ዓላማ የሚወጡ ሪፖርቶችን አይቀበልም። ከ2013 በኋላ የወጡ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሪፖርቶች ደግሞ እንዳጋጣሚ ሆኖ መንግስት ከማይቀበላቸው ጎራ የሚመደቡ ናቸው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ከእውነተኛ የሰብአዊ መብት መከበር ፍላጎት መንፈስ ያልመነጨውን ይህን ሰነድ ውድቅ ለማድረግ ተገድዳለች ።

ከላይ የተጠቀሰው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ላወጣው ሪፖርት የኢፌዴሪ መንግስት የሰጠውን ምላሽ ጠቅለል አድርገን ስንመለከት፣ "ከዚህ ቀደም በየአመቱ የሚያወጣው እንዳለ የተደገመበት፣ አዳዲሶቹም ያልተረጋገጡ፣ ተአማኒ በሚል የቀረቡት የመረጃ ምንጮችም ገለልተኛ ያልሆኑና ሕገመንግስታዊ ስርአቱን በኃይል ለመናድ የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ታዋዋሚዎች ናቸው የሚል ነው። ዓላማውም የሰብአዊ መብት አያይዝን ለማሻሻል በአሜሪካና በኢትዮጵያ

መሃከል የሚደረገውን የሁለትዮች የሃሳብ ልውጥ ማደናቀፍ ነው።" የሚል ነው። በዚህ ምክንያት እንደማይቀበለውም ነው ያስታወቀው።

የኢፌዴሪ መንግስት የሰብአዊ መብት አያያዝን ለማሻሻል ከአሜሪካ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ዓለም አቀፍ ባለድርሻ አካላትም ጋር ይሰራል። በዚህ የጋራ አሰራር የሰብአዊ መብት ጥበቃን የሚያሻሽሉ ተግባራትንም አከናውኗል። ለዚህ አስረጂነት በቅርቡ ይፋ የሆነውንና ተግባራዊ መደረግ የተጀመረውን ብሄራዊ የሰብአዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር መጥቀስ ይቻላል፡፡

በቅርቡ ተግባራዊ መሆን የጀመረው ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው ብሄራዊ የሰብአዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር የማዘጋጀት መነሻ እ.ኤ.አ በ1993 ዓ/ም በተካሄደው 2ኛው የቪየና የዓለም የሠብአዊ መብት ኮንፈረንስ ላይ በአገራት መሃከል የተደረሰበት መግባባት ነው። የዚሁ ኮንፈረንስ ውጤት የሆነው "የዲክላሬሽንና ትግበራ ፕሮግም" ክፍል ሁለት አንቀፅ 7 ሃገራት የሠብአዊ መብቶችን በማስፋፋት፣ በማስጠበቅና በማረጋገጥ ረገድ ያላቸውን አፈፃፀም ወደተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ሊወስዱት የሚገባውን እርምጃ በግልፅ የሚያመለክት ሀገር አቀፍ የሰብአዊ መብት የድርጊት መርሃ ናግብር የማዘጋጀት አስፈላጊነትን አስረግጦ ያሳስባል። የኢፌዴሪ መንግስት በዚህ መሰረት የብሔራዊ የሠብአዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል። የኢትዮጵያ መንግስት ይህን ሰነድ በማዘጋጀትና በዓለም አቀፍ ደረጃ መግባባት የተፈጠረበትን ጉዳይ መፈፀም ዓለም አቀፍ ኃላፊነትን መወጣት  መሆኑን ያምናል፡፡

በተመሳሳይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ካውንስል፣ ሀገራት ሰብአዊ መብትን በማረጋገጥ በኩል ያላቸውን አፈፃፀም የሚገመግምበት በየአራት ዓመቱ የሚካሄድ ሁሉ አቀፍ የግምገማ መድረክ አለው። ኢትዮጰያም "ዩኒቨርሳል ፔረዮዲክ ሪቪው" ተብሎ ለሚጠራው ለዚህ የግምገማ መድረክ  ሪፖርት አቅርባለች። በዚህ ኢትዮጵያ ለመድረኩ ባቀረበችው ሪፖርት ላይ በመመስረት ከተሰጡትና ሃገሪቱ ከተቀበለቻቸው አስተያየቶች መሃከል "የሰብአዊ መብት ድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀትና ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ " የሚለው ይገኝበታል።

ይህን የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት፣ ሰብአዊ መብትን በይበልጥ ለማረጋገጥ በመንግስት ረገድ ያለውን ፖለቲካዊ ቁረጠኝነትና ፈቃደኝነት ማረጋገጫ ከመሆኑም በተጨማሪ በ"በዩኒቨርሳል ፔሪዮዲክ ሪቪው" ላይ ለኢትዮጵያ መንግስት የተሰጡን አስተያየቶች የመፈፀም አካል ነው። ይህን ሰነድ ማዘጋጀትና መተግበር በራሱ ኢትዮጵያ በአለም አቀፉ ማህበረሰብ የተጣለባትንሰበአዊ መብት የማስከበር ሃላፊነት እየተወጣች መሆኑን ያመለክታል።

መንግስት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ላወጣው ሪፖርት በሰጠው ምላሽ፣ "መንግስት የሕገመንግስቱን ድንጋጌዎች በማክበር ግዴታውን ይወጣ ዘንድ የሚደረግለትን ማንኛውንም ድጋፍ ለመቀበል ዝግጁ ነው።" ሲል የገለፀው በሰብአዊ መብት አያያዝ ዙሪያ ከአሜሪካም ጋር የሚያደርገው ውይይት ዓላማ የቪየና የዓለም የሠብአዊ መብት ኮንፈረንስና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ካውንስል ዩኒቨርሳል ፔሪዮዲክ ሪቪው ላይ ገንቢ ሃሳቦችን እንደተቀበለው ሁሉ ገንቢ ሃሳብ ለማግኘት ያለውን ፍላጎት እየገለፀ ነው።

ይሁን እንጂ የሰሞኑ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ያወጣው ሪፖርት ከዚህ ውጭ የሆነ ዓላማ ያለው ይመስላል። የኢፌዴሪ መንግስት በምላሹ "ከተሟላ የሰብአዊ መብት አያያዝ አንጻር ሲገኝ የሚቀርብበትን ተገቢ ትችት ለመቀበል ዝግጁ የሆነውን ያህል፣ ሆን ተብሎ ገፅታውን ለማበላሸት ዓላማ የሚወጡ ሪፖርቶችን አይቀበልም። ከ2013 በኋላ የሚወጡ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሪፖርቶች ደግሞ እንዳጋጣሚ ሆኖ መንግስት ከማይቀበላቸው ጎራ የሚመደብ ነው።" ሲል የገለፀው ይህንኑ ለማመልከት ነው።

የኢፌዴሪ መንግስት ቀደም ሲል በተነሱት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት አያያዝ መድረኮች ላይ ያገኘውን ገንቢ ሃሳብ መነሻ በማደረግ ያዘጋጀውን ብሄራዊ የሰብአዊ መብት አያያዝ መርሃግብርን በ2006 ዓ/ም ተግባራዊ የሚያደርግበት የድርጊት መርሃ ግብር ቀረፆ እያስፈፀመ ይገኛል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሠብአዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር ዋና ዓላማ፤ በሃገር አቀፍ ደረጃ በተቀናጀና ከሌሎች እቅዶች ጋር በተጣመረ አኳኋን፣ በሕገመንግስቱ ለተረጋገጡት የዜጐች ሠብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የበለጠ

ጥበቃ የሚያበጁ ሥልቶችና አቅጣጫዎችን መቀየስ ነው፡፡ መርሃ ግብሩ የኢትዮጵያን አጠቃላይ የሠብአዊ መብት አጠባበቅ በመዳሰስ መሻሻልና መስተካከል የሚገባቸውን ጉዳዮች በመለየት የሚሻሻሉበትንና የሚስተካከሉበትን አቅጣጫዎች ይተልማል። በዚህ ትልም መሰረት የሚያስፈፅማቸውን ዝርዝር አላማዎች አስቀምጧል። እነዚህ ዝርዝር ዓላማዎች፤

1. የዴሞክራሲና የሠብአዊ መብቶች ባሕል የሚያጎለብቱ ሥትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ማመልከት፡፡
2. ለሚቀጥሉት ሦስት አመታት በሃገሪቱ የተቀናጀና ቀጣይነት ያላቸውን የሠብአዊ መብቶች የማስከበሪያ አቅጣጫዎችን ማመልከት፡፡
3. የሠብአዊ መብቶች የግንዛቤ ማስፋፊያ ሥራዎች የሚካሄዱበትን ሥልቶች ማመልከት፡፡
4. ሠብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማስከበሩና በማረጋገጡ እንቅስቃሴ መንግሥት በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 እና ሌሎች ሁኔታዎች በሠብአዊ መብት ዙሪያ እንዲንቀሳቀሱ ከተፈቀደላቸው የበጎ አድራጐት ድርጅቶች ማህበራት በተለይም ከብዙሃን ማህበራትና ከአለም አቀፉ ሀብረተሰብ እንዲሁም ከልማት አጋሮች ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት የሚችሉበትን አቅጣጫዎች ማመልከት፡፡

የሚሉ ናቸው።

የሰብአዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብሩ መድረሻ ግቡንም አስቀምጧል። ይህም በኢፌዴሪ ሕገመንግስት ዋስትና ያገኙትን የሠብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማስከበር፣ በማስፋፋትና በማሟላት ረገድ ሲከናወኑ የነበሩትን ፍሬያማ ተግባራት በዚሁ ብሔራዊ ሠነድ አማካይነት በተቀናጀና በተዋሃደ መንገድ እንዲጠናከሩ በማድረግ የዜጎችን ሠብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብተቶች በተሻለ ሁኔታ ማረጋገጥ ነው።

ይህ ዕውነታ  ኢትዮጵያ ለሰብአዊ መብት መከበር ያላትን ቁርጠኝነትና ለዚህ ያከናወናቸውን ጥረቶች፣ እንዲሁም በውይይት ገንቢ ሃሳቦችን ለመቀበል ያላትን ፍቃደኝነት ያመለክታል። ይህንና በዚህ ጥረት የተገኙትን ውጤቶች ለዘነጋው የአሜሪካ

የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ያወጣው ሪፖርት መንግስት በፅሁፉ መግቢያ ላይ የጠቀሰኩትን ምላሽ ሰጥቷል፤ “ገንቢ ያልሆነ ትችት የቀረበበት ሪፖርት” የሚል ምላሽ፡፡

ይህን የኢትዮጵያ መንግስትን ምላሽ የተመለከቱ ዜጎች “የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ ሪፓርት ይዘት ምንድነው? በምን ሁኔታ ነው መሰረተ ቢስ የሆነው?” የሚል ጥያቄ ማንሳታቸው አይቀሬ ነው። በመሆኑም በዚሁ ርዕስ በሚቀርብ ክፍል ሁለት ፅሁፍ ከሪፖርቱ ውስጥ የተወሰኑትን እንመለከታለን።